# የተመረጡ ፍርዶች

(በአሰሪ እና ሠራተኛ ህግ ላይ ያተኮሩ)

የሰ/መ/ቁ. 46075

ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች፡-*** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ንጉሴ ሀዱሽ አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ዲን አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የግራቀኙን ከስራ ቅጥር የመነጨን ክርክር የሚገዛ የትኛው ህግ ነው የሚለውን ለይቶ ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በተጠሪ ጽ/ቤት በሻሂ ማሽን ሠራተኝነት በደመወዝ ተቀጥሮ ሲሰራ የቆየ ለመሆኑ እና በመጨረሻም ተጠሪ በሰጠው ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ ለመሆኑ ተጠሪ የካደው ጉዳይ አይደለም፡፡

በዚህ መነሻ በተጠሪ በኩል የተፈፀመው የሥራ ስንብት የአሰሪና ሠራተኛ ህግ ከደነገገው ውጭ ስለሆነ ልዩ ልዩ ክፍያ ይገባኛል በማለት የአሁን አመልካች ለቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በጥሪው መሰረት የበኩሉን መልስ ለማቅረብ አልቻልም በሚል ምክንያት ክሱ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን የክስ አቤቱታ እና እንደ አቤቱታው ለማስረዳት ያቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ ተመልክቶ በግራቀኙ መካከል የስራ ቅጥር ግንኙነት እንዳለ እና ከዚህ የቅጥር ግንኙነት የተነሳው ክርክር የሚዳኘው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት መሆኑን ገልፆ ሠራተኛው ለቀጣሪው ከሰጠው የአገልግሎት ዘመን አንፃር ሊሰጠው የሚገባው የአንድ ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ብቻ ሆኖ አልተገኘም የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ሥርዓቱ የተሟላ ሆኖ አልተገኘም ስለሆነም ከአዋጅ

አንቀፅ 35/1/ለ/ አንፃር ሲታይ ስንብቱ ህግ ከደነገገው ውጭ ሆኖ ተገኝቷል በማለት ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡
በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁኑ ተጠሪ በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሯል፡፡
ዋነኛ የይግባኝ አቤቱታውም የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የሚተዳደረው በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በደንብ ቁጥር 61/99 መሠረት በመሆኑ ዩኒቨርስቲው ተከራካሪ የሆነበትን ይህን መሰል ጉዳይ በሚተዳደርበት አዋጅ መሠረት እንጂ በአሰሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ አይደለም የሚለው ይገኝበታል፡፡
ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአሁን ተጠሪ እንደሚለው ጉዳዩ በአሰሪና ሠራተኛ ህግ የሚዳኝ አለመሆኑን የስር ፍ/ቤት ተገናዝቦ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 9 እና 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ነበረበት በሚል ምክንያት ተችቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አለማግኘቱ ገልፆ ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውን የሰበር አቤቱታ የአሁን አመልካች አቅርቧል፡፡
የሰበር ቅሬታው ይዘትም የስር ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳይ የወሰነው የአሁን ተጠሪ በሌሉበት ስለሆነ ይህ ተጠሪ በዚያው ጉዳይ ተከራካሪ ለመሆን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 78 መሠረት በክርክሩ እንዲገባ ካልተደረገ በቀር በቀጥታ የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት የለውም ይህም ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አላየውም እኔን የቀጠረኝ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ሲሆን የተቀጠርኩበት ለሻሂ ክበብ በሻሂ ማሽን ሰራተኝነት ነው የምሰራበት ክበብ በራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደር በተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ቁጥጥር የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በቀጥታ በአዋጅ ቁጥር 515/99 ሆነ በደንብ ቁጥር 6199 የሚገዛ የሚሸፈን አይደለም የሚለውን በግራ ቀኝ መካከል ለተነሳው የህግ ጥያቄ መነሻና አንኳር የሆነውን ክርክር አቅርቧል፡፡
በዚህ የሰበር አቤቱታ ላይ ያሁን ተጠሪ ቀርቦ የበኩሉን ክርክር ማቅረብ ይችል ዘንድ መጥሪያ ተልኮለት መጥሪያው የደረሰው ለመሆኑ በራሱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ እንደጠሪው ለመደመጥ መብቱ ሊጠቀም አልቻለም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በተጠሪ በኩል በተጠቀሱት አዋጆች ለግራቀኞችን የቅጥር ሁኔታ ተፈፃሚነት የላቸውም በማለት በቀረበው ክርክር በተጠሪ በኩል ሊቀርብ የሚችል ማስተባበያ ካለ ባከራካሪ ነጥብነቱ

ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት መስጠት አልቻለም የተለየ ማስተባበያ እስካልቀረበ ድረስም አመልካች እንዳለው እንዲያገለግል የተቀጠረበት የሻሂ ክበብ በራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደር ከሆነ ከዚህ መሰል ቁጥር የመነጨን ክርክር ተጠሪ የጠቀሳቸው ህጎች የማይገዙ ይልቁንም ክፍተቱ ባሰሪና ሰራተኛ ህግ የሚሸፈን ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ስለተገኘ ወይም ለዩኒቨርስቲው የህ/ሰብ ክፍል አገልግሎት ስለሰጠ ብቻ በደፈናው በሲቪል ሰራተኛ አስተዳደር ህግ ይገዛል ለማለት የሚያበቃ አለመሆኑ እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጉዳይ ባሰሪና ሰራተኛ ህግ የሚገዛ አይደለም በዚህም ሳቢያ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው የውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>***ው ሣ ኔ***</u>

1. የክልሉከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 7229 በ19/6/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የትግራይ ክልል ጠቅላላ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29531 በ30/07/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከሥራ ቅጥር የመነጨውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሥልጣን ባለው የወረዳ ፍ/ቤት ታይቶ ዳኝነት የተሰጠበት ስለሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ስልጣን የመ/ቁጥር 7229 አንቀሳቅሶ በሌላው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መልሰናል፡፡ ግልባጩ ይድረሰው፡፡

አመልካች ለዚህ ክርክር ያወጣውን ወጭ በእራሱ ይሸፍን ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

የሰበር መ/ቁ 49931

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሸገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር፤ ጠበቃ ምክሩ ወልደአረጋይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተሰማ ኃይሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ጋር ህዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በመሰረቱት የስራ ውል በድርጅቱ የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልፀው የስራ ውሉ ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም ከህግ ውጪ መቋረጡን ጠቅሰው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ የሞባይል ስልክ አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈል ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ያሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ክርክር ተጠሪ የስራ መሪ ስለሆነ የስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ በስራ አፈፃፀም ላይ ባሳዩት ጥፋትና የብቃት ማነስ ችግር የተሰናበቱ በመሆኑ እርምጃው ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ለማየት ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ዋናውን ክርክርም ተመልክቶ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ አመልካች የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ የስራ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱ ባጭሩ ተጠሪ በስራቸው ላይ የብቃት ማነስ ያሳዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ከህግ ውጪ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባቡ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ በብቃት ማነስ ምክንያት ለስራው ብቁ አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪም በተደረገላቸው መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የስራ ስንብቱን እርምጃ ህጋዊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ገልፆ ማስረጃ ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡት ማስረጃዎች የአመልካች ምክንያት በአሳማኝ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ችሎት ስልጣኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በህግ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሲፈፀሙ ማቃናት ነው፡፡ ይህም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ነበር የተባለው የስራውን አሰራር የሚገልፅ ነው በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የደመደሙት ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱም አመልካች የተሳሳተ ነው ብሎ ቢከራከርም ተጠሪ ሪፖርቱ በሰነድ ችግር ያልተሟላ ስለመሆኑ በመግለፅ ለአመልካች የገለጸ መሆኑን አረጋግጠው ሂሳቡ የተሳሳተ ነበር ለማለት ያልቻሉ መሆኑን ያመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ

ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ ሲደረግ በጭብጥነት ያልተያዘውን ተጠሪ በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት በአማራጭ አመልካች በመልስ መልሱ ላይ ጠይቋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ምክንያት ይሆናል ያለው ነጥብ ተጠሪ ለአለቃ የማይታዘዙ ናቸው የሚለው ሆኖ በስር ፍርድ ቤቶች የክርክር ነጥብ ያልሆነ እና በተገቢው ማስረጃም ያልተረጋገጠ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ወደ ስራ ከሚመለስ በአማራጭ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ምክንያት የሚደረገው በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር የሚከሰት መሆኑን ፍር ቤቱ ሲያምን ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገባል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊኖር ይገባል፡፡ ያለበቂ ማስረጃና ምክንያት አሰሪ የስራ ግንኙነቱ ችግር ውስጥ ሊወድቅ ይቻላል ብሎ ስለተከራከረ ብቻ ድንጋጌውን ተግባራዊ ማድረግ የስራ ዋስትናን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14112 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80323 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 59666

ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

***ዳኞች፡-*** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

ኡዳነ ንጉሴ

***አመልካች፡-*** የኦሮሚያ መንገድ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ሡላማዊት ኃይሉ ቀረቡ፡፡

***ተጠሪዎች፡-*** አቶ አቡ ጎበና ከጠበቃቸው ከአቶ ተካልኝ ነጋሣ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በአሁኑ የሰበር ተጠሪ አቅራቢነት ለስር ወረዳ ፍ/ቤት ነሐሴ 27 ቀን 1999 ዓ.ም የቀረበው ክስ በተከሳሽ /በአሁኑ አመልካች/ መ/ቤት ከ1989 እስከ የካቲት 1999 ዓ.ም በተለያዩ የሥራ መደቦች በወር 2110 ደመወዝ እየተከፈለኝ ከቆየሁ ነኃላ ተከሳሹ ከስራ ሲያሰናብተኝ የአገልግሎት ካሳ እና የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ብር 13,187.50 ካሰበልኝ በኃላ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ታክስ ብር 2,203.87 ከቀነሰ በኃላ በስልጣኑ ለት/ቤት የከፈልኩት ነው በማለት ብር 6,792.57 ቆርጦብኝ ብር 4,191.04 ብቻ ከፍሎኛል፡፡ የከፈለኝን ገንዘብም ቢሆን መከፈል ከሚገባው ጊዜ 2 ወር በማዘግየት የሚያዝ የሚያዚያ ወር 1999 ዓ.ም በመሆኑ በአሰራርና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 337/96 በአንቀፅ 36 በተደነገገው መሠረት በ7 ቀን ውስጥ አልከፈለም፡፡ የት/ቤት ክፍያም ቢሆን በህብረት ስምምነታችን አንቀፅ 25 ከ12ኛ ክፍል በላይ ለሆነ ትምህርት የት/ቤት ክፍያ ተከሳሽ መ/ቤት 50% እንደሚከፍል ተገልጽዋል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ መ/ቤት ያለአግባብ የቆረጠብኝ ገንዘብና ክፍያ ባዘገየበት የ3 ወር ደመወዜን እንዲከፍለኝ ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሹም በነገረፈጁ አማካኝነት በሰጠው መልስ ከሳሽ ለ11 ዓመት አገልግያለሁ የሚለው ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ከሳሽ ከመስከረም 1 ቀን 1989 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1992 ድረስ የመንግስት ሰራተኛ ነበረ፡፡ የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ ደግሞ በአሰሪና

ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 ጥቅማጥቅም ማግኘት አይችልም፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ መ/ቤት የተቀጠረው ከሐምሌ 1 ቀን 1992 ጀምሮ ስለሆነ የአገልግሎት ካሳ ማግኘት ያለበት ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከሳሽ በጊዜው የት/ቤት ክፍያ እየጠየቀ ተከሳሽ መ/ቤት ሲከፍል የቆየ በመሆኑ በመካከላችን ውል የለም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ከዚሁ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ለ/ ስር የተጠቀሰው ግዴታ አልተወጣም በማለት የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

የስር ወረዳ ፍ/ቤትም ዕዳን አንድ ሠራተኛ ከሚያገኘው የአገልግሎት ካሳ ማቻቻል አይቻልም፡፡ ተከሳሽ አለኝ የሚለው መብት ካለ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት መጠየቅ እንጂ ከደመወዙ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ነገር ላይ ማቻቻያ ሊደረግ አይገባም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ተከሳሽ ከሳሽ ደመወዝ መቁረጡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1833/11/ የተደነገገውን የሚፃረር ነው በማለት ተከሳሽ ከከሳሽ የቆረጠውን ገንዘብ ብር 6,792.57 ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝና ኪሳራ ብር 500 እንዲሁም የጠበቃ አበል 10% እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ይግባኝ ባይ /የሥራ ተከሳሽ/ የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሳ ለመልስ ሰጪው ከከፈለ በኃላ የ11 ዓመት አገልግሎት በተከሳሽ መ/ቤት የለውም ሲል የተከራከረው ያለአግባብ ነው፤ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪውን ያስተማረ ቢሆንም ምን ያህል እንደሚያገለግል የተማረው መቼ እንደሆነና ግዴታውን ተወጥቷል የሚባለው መቼ ነው የሚሉትን ነጥቦች ያላስረዳ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የሚነቀፍ ነገር የለም በሚል ውሳኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካች ለሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል በማመልከቱ የሥር ሰበር ሰሚው ችሎትም የግራቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኃላ ከአገልግሎት ካሳ ክፍያ ውስጥ ለትምህርት የተከፈለውን በሚመለከት ተመላሽ የሚያደርግ ስለመሆኑ ውል መኖር አለበት፡፡ ውል በሌለበት አስተማርኩ በሚል ብቻ ከአገልግሎት ካሳ ቆርጦ ማስቀረት ተቀባይነት የለውም፡፡ ክፍያ ለዘገየበት አመልካች ያመነውን ያልከፈለ ስለሆነ በክፉ ሀሳብ ተጠሪን

ለመጉዳት አዘግይቷል ለማለት አይቻልም በማለት አመልካች ለተጠሪ የ3 ወር ደመወዝ መክፈል የለበትም ሲል የሥር ፍ/ቤት ውሴኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ቅር የተሰኘው የበር አመልካችም ለዚህ ችሎት ባቀረበው ቅሬታ ተጠሪው ከመስከረም 01 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 1992 ዓ.ም ድረስ በአመልካች መ/ቤት ያገለገለው በአሰሪና ሠራተኛ ህግ መሠረት ሳይሆን በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ በመሆኑ የሦስት ዓመት ከአሥር ወር የአገለግሎት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈለው አይገባም፡፡ ተጠሪው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀው የ2ኛ ዲግሪውን ትምህር መንግስት እየከፈለ ትምህርቱን እንዲጠናቀቅ የሚፈለግበትን አገልግሎት ሳይፈፅም በመሆኑ በተሸሻለው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ መሠረትና አንቀጽ 39/ሸ/ የውል ግዴታ ስላለበት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ የለም፣ ገንዘቡም ለመንግስት ተቆርጦ ገቢ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ምንም ዓይነት ስምምነት ከአመልካች ጋር የለኝም በሚል ያቀረበው ክርክርም ቢሆን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 26 በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ባለመፈረሙብቻ ግዴታውን የሚያስቀርለት አይሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ እስከአሻሻለው ድረስ የጠበቃ አባል 10% እና ኪሳራ ብር 500 አሻሽሎ መወሰን አልያም መሰረዝ ይገባው ነበር በማለት ከመስከረም 1 ቀን 1989 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ያለውን የ3 ዓመት ከ10 ወር ያገልግሎት ካሳ አመልካች ለተጠሪው ይከፈላል የተባለው እንዲሰረዝ አመልካች ከተጠሪው ያገልግሎት ካሳ ውስጥ ለትምህርት የከፈለውን ቆርጦ ማስቀመጡ ያላግባብ ነው የተባለው ተሽሮ ገንዘቡን ለአመልካች ገቢ እንዲሆን እንዲወሰን፣ አመልካች ለተጠሪው እንዲከፈል የተወሰነበትን የጠበቃ አበል እና ኪሳራ እንዲሰረዝ ጠይቋል፡፡

አመልካች ላቀረበው የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ከመስከረም ወር 1989 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ያገልግሎት ካሳ አስቦ ይከፈለኝ እራሱ ያሁኑ አመልካች ስለሆነ ተጠሪ ክስ ከመሰረትኩበት በኃላ ያገልግሎት ካሳው የተከፈለው በስህተት ነው ብልም ከመስከረም 01 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ሰራተኛ ስለመሆኔ በስር ፍ/ቤት በቀረበው የፅሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 26/2/ ከትምህርትና ስልጠና በተያያዘ የውል ግዴታ መግባት እንደሚያስፈልግ ይናገራል፡፡ ተጠሪም የውል ግዴታ ገብቻ

የፈረምኩት ሰነድ የለም፡፡ አመልካችም በማስረጃነት ያቀረበው ሰነድ የለም፡፡ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 39/1/ሸ/ ከስልጠና ጋር በተያያዘ የአሰሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ስራውን በገዛ ፍቃዱ ሰራተኛው ሲለቅ ያገልግሎት ካሳ እንደሚከፈለው ይደነግጋ፡፡ በመሆኑም የሰበር ተጠሪው ካሰሪው መ/ቤት ጋር የገባሁት የትምህርት ውል ስለሌለ የአገልግሎት ካሳ ከማግኘት የሚከለክለኝ ነገር የለም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የቀረበ ሲሆን እኛም በስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ለተጠሪ ሊከፈለው ይገባል በሚል በተወሰነው ገንዘብ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚለው በአገልግሎት ካሳ በጠበቃ አመል እና በኪሳራ ገንዘብ አከፋፈል ነው፡፡

የአገልግሎት ካሳን በሚመለከት ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠር እና ያገልግሎት ካሳ ለተጠሪው ይገባል በማለት አመልካች ከወሰነው ገንዘብ ውስጥ አመልካች ለተጠሪው የት/ቤት ክፍያ ፈፅሜያለሁ በማለት የቀነሰው ገንዘብ ነው፡፡

ተጠሪው ከመስከረም 1989 እስከ የካቲት 1999 ዓ.ም ለ11 ዓመት በአመልካች መ/ቤት ማገልገሉን በመጥቀስ ሲከራከር አመልካች ግን ተጠሪው ከ1989 መስከረም ወር ጀምሮ እስከ 1992 ሰኔ ወር ድረስ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/96 የማይተዳደርና የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሰራተኛ ነበር በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ የተነሳ የ3 ዓመት ከ10 ወር የአገልግሎት ካሳ አይገባውም ብሏል፡፡ ይሁን እንጅ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች መ/ቤት ቀደም ሲል በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ የሚተዳደር የነበረና ከዚያም በአዋጅ ቁ. 377/96 ማለትም ስለ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ በወጣው አዋጅ እንዲተዳደር መደረጉን ነው፡፡ ተጠሪም ቢሆን ቀደም ሲል በአመልካች መ/ቤት የመንግስት ሠራተኛ የነበረ ሲሆን አመልካች መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 እንዲተዳደር ሲደረግ ተጠሪውም በተመሳሳይ ሁኔታ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 377/96 እንዲተዳደር ሲደረግ ተጠሪውም

በተመሳሳይ ሁኔታ በተጠቀሰው አዋጅ የሠራተኛን ትርጉም በማሟላት በአመልካች መ/ቤት ማገልገሉን በማመን የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሳ በማስላት አቃላይ የሚከፈለው የአገልግሎት ካሣ መጠን ከታወቀ በኃላ ለትምህርት ቤት የከፈለውን በመቀነስ ለራሱ አስቀርቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሠሪው ማለትም ያሁን አመልካች የተጠሪው የአገልግሎት ዘመን 11 ዓመት መሆኑን ተቀብሎ ምን ያህል የካሣ መጠን እንደሚከፈለው ካረጋገጠ በኃላ በፍ/ቤት በተጠሪ ከሳሽነት ክስ ሲቀርብ የተጠሪውን ቀደም ሲል የመንግስት ሠራተኛ ነበር በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የአገልግሎት ካሣ ማግኘት ያለበት ከሐምሌ 1992 ጀምሮ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ ውጤት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን የአገልግሎት ዘመን በሁለት በመክፈል ካሣ ሊከፈለው የሚገባው በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መተዳደር ከጀመረበት ጊዜ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ያልተቀበለው በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪው 11 ዓመት አገልግሎት አለው ተብሎ በዚሁ መጠን የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሳ ሊከፈለው አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ውድቅ በማድረጉ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ከዚህ ከካሣ አከፋፈል ጋር ተያይዞ የሚነሳው አመልካች ለተጠሪው የሚገባውን የካሳ መጠን በስሌት ካረጋገጠ በኃላ የተጠሪው 2ኛ ዲግሪ ሲማር አመልካች ለት/ቤት የከፈለውን ገንዘብ የቀነሰው ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኃላ በአመልካች መ/ቤት ማገልገል ሲገባው ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለት/ቤት ያወጣውን ወጪ ከተጠሪው ለመቀበል በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሸ/ መሠረት መብት አለው ምክንያቱም በአመልካችና ተጠሪ መካከል የውል ግዴታ አለ የሚል ነው፡፡ የውል ግዴታውም ሊመሠረት የቻለው ተጠሪው የትምህርት ቤት ክፍያ እንዲከፍልለት በየጊዜው እየጠየቀ አመልካችም ይከፍልለት ነበር በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከአመልካች አለ የሚለውን የውል ግዴታ ተጠሪው የፈረምኩት ሠነድ የለም በማለት ይከራከራል፡፡

እዚህ ላይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የትምህርት ቤት ክፍያን በሚመለከት ውል አለ ወይስ የልም? የሚለውን ነጥብ ሳይሆን አመልክች ለተጠሪው ከሚገባው የአገልግሎት ካሣ የትምህርት ቤት ክፍያ ቆርጦ ማስቀረት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ነጥብ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተገለፀው አመልካችና ተጠሪ የሚተዳደሩት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሲሆን የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች በአዋጁ የተቀመጡትን መብትና ግዴታ ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በአዋጁ ከተጠቀሱት መብቶች አንዱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ደመወዙንና ከደመወዙ ጋር የተያያዙትን ክፍያዎችን በህጉ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ክፍያው አከራካሪ ሆኖ ከተገኘ የህጉን አካሄድ መከተል የግድ ይላል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የመንግስት ግብር ተቀንሶ ተጠሪው የአገልግሎት ካሣ ማግኘት ያለበት ብር 10,983.63 መሆኑን ሲገልጽ ይኸንኑ የገንዘብ መጠን አመልካችም ትክክል መሆኑን ያምናል፡፡ ይሁን እንጅ የት/ቤት ክፍያ ብር 6,792.57 መቀነሱ አግባብ ነው ይላል፡፡ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ደመወዝ የሚቀነሰው በህግ በህብረት ስምምነት ወይም በስራ ደንብ በተወሰነው ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ መሠረት ካልሆነ ወይም ሠራተኛው በጽሁፍ ካልተስማማ አሰሪው ከሠራተኛው መቀነሥ እንደማይችል ወይም በዕዳ ሊይዝ ወይም ሊያቻችል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ የአገልግሎት ካሳም ቢሆን ለዕዳ የሚያዝ ወይም የሚቀነስ ከሆነም በተጠቀሰው የህግ አንቀጽ መሠረት መቀነስ ወይም ሊያዝ ከሚችል ውጪ አሠሪ በራሱ ውሳኔ ሊቀንስ ሊይዝ ወይም ለዕዳ እንዲቻቻል ማድረግ አይችልም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሰበር አመልካች ቆርጦ ያስቀረው የአገልግሎት ካሣ ገንዘብ ለተጠሪ እንዲመልስ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡ ሌላው አመልካች እንደመሠረታዊ የህግ ስህተት የጠቀሰው የጠበቃ አበል 10% አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተጠሪው ክርክር ያካሄደው በግሉ ስለመሆኑ አልተከራከረም፡፡ ነገር ግን 10% ለጠበቃው አበል መወሰኑ አለአግባብ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ጠበቃው ሙያዊ አገልግሎት መስጠቱ እስካልተካደ ድረስ ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 42 በተደነገገው መሠረት ተገቢና ሚዛናዊ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ተገቢና ሚዛናዊ ክፍያ ነው የሚባለው ደግሞ በተጠቀሰው የህግ ቁጥር ከንዑስ ቁጥር 1-8 የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ የተወሰነ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች ግን የሥር ፍ/ቤት 10% የጠበቃ አበል ሲወስን በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 ሥር የተዘረዘሩ መመዘኛዎች የተጣሱ ስለመሆናቸው ያቀረበው የህግ ክርክር የለም፡፡ ይህ

ችሎትም የቀረበውን የጠበቃ አበል ቅሬታ ከተጠቀሰው ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 462ና 463 ድንጋጌ ጋር እንዳገናዘበው በደንቡ የተዘረዘሩት መመዘኛዎች የተጣሱ ስለመሆናቸው አመልካች የሚሆን ነገር አላገኘም፡፡ በመሆኑም በጠበቃ አበል አወሣሠን ላይ በሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የለም፡፡

አመልካች ያቀረበው ሌላው ክርክር የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሥረ ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በማሻሻል እስከወሰን ድረስ የብር 500 /አምስት መቶ/ ኪሣራ መቀነስ ወይም መሰረዝ ነበረበት የሚል ሲሆን ይህ ችሎት ተጠሪ በክርክር ወቅት ከብር 500 (አምስት መቶ) ያላነሠ ኪሣራ እንደሚደርስበት ያምናል፡፡ የኪሣራው መጠን ከዚህ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ያንሣል ቢባል እንኳን የአመልካች ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን በጎላ መልኩ የሚጎዳ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አሻሽሎ በመወሰኑ ብቻ ኪሣራ መቀነስ አለበት ወይም ሙሉ በሙሉ መሠረዝ አለበት ለማለት ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ሰበር ሰሚው ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔን አሻሽሎ ሲወስን ኪሳራውን ግን በማጽናቱ የተጣሰ ህግ የለም፡፡ ስለሆነም በኪሣራ አወሳሰን አሻሽሎ ሲወስን ኪሳራውን ግን በማጽናቱ የተጣሰ ህግ የለም፡፡ ስለሆነም በኪሣራ አወሣሠን ረገድም የሥር ፍ/ቤት የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 90368 በቀን 14/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፣ በውሳኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሏል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***